ፖለቲካና ኦርቶዶክሳዊያን

ወቅታዊ የፖለቲካ ምክኒያተ-ተሳትፎ እና ግቡ

መጋቢት ፭ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም.
አዲስ አበባ

በዓለም ዙሪያ ለአስተዳደርና ፖለቲካ፣ ለማኅበራዊና ለአውቀት መሠረት የጣለችው ቤተልርስቲያን ናት። በአውሮጳ የኑፋቄ ትምህርት የፈጠረው የግራ መጋባት ውስጥ የተወለደው የአብርሖት ፅንሰ አሳብ ለሃይማኖት የጠላትነት ዝንባሌ ያዳበረው በዚህ አውድ ውስጥ ነው። ሩሲያ ተሻግሮ፣ ኢትዮጵያ መጥቶ፣ ግብጽና ሶሪያን ደምስሶ አሁን የመንገኝበትን እምነትን ከፐለቲካ፣ ሕዝብን ከሕዝብ ለይቶ የማስተዳደር፣ ቅኝ የማድረግ፣ የወረራና የባርነት ሥርዓት መዘርጋትም የተስፋፋው በኑፋቄ፣ በስሁት ሰብአዊ ፍልስፍና እየተመራ ነው።

አሁን የምንገኘው አፍሪካ ምነነቷን ጥላ፣ በእርዳታ ሰጭነትና በፈቃድ ባርነት በሚስተዳድሯት በዘመነ አብርሆት በተገኙ ባዕዳን እሳቤ ነው። የሃይማኖት መምህራንና አባቶችም በግላቸው ከቅጣትና ከመከራ ለማምለጥ ፀረ ኦርቶዶክስ ከሆነው የአስተዳደርና የፖለቲካ ፍልስፍና ጋር ተስማምተው እንደ ምዕረባዊያን የሴኩላር ሊቅ ‘መቻቻል” እያሉ ለአውነት መመስከርን ችላ ብለዋል።

ጊዜው ክርስቲያኖችም ሆኑ ለሕሊናቸው ክብር የሚሰጡ የባህል አባቶች ሁሉ በአንድነት ቆመው ሐሰትንና የባዕዳንን ፀረ-አገር ፈለቅ እውትና እምነት የፖለቲካ ርእዮት ማስቆም አብረን የምንቆምበት ነው። ንጉሥ አንቀው፣ ጳጳስ ሰቅለው፣ በጎሣ ሰፈር ከልለቅ፣ ራሳቸውን ነፃ አውጭ ብለው ሰይመውና በዘረኝነት ታውረው ወደ አራዊትነት የተለወጡትን ጥቂት ሴኩላር ምሑራን እየተከተሉ የሚያልቁ ሚሊዮኖችን መታደረግ የሁሉም ጤናማ ዜጋ ግዴታ የሆነበት ዘመን ላይ አንገኛለን። ፖለቲካውን ይዘው እንምራችሁ የሚሉን ሰዎች በየደረጃው ሲመዘኑ እግዚአብሔርን የማይፈሩ፣ ሕለናቸውን የማያከብሩ፣ ታላላቅ የእምነትና የባህል አባቶችን የማያፍሩ፣ ከባሕር ማዶ ባገኙት የሥህተት ፍልስፍና የሚመሩ፣ በቅዠትና በሕልም መካከል ያለውን ልዩነት የማይመረምሩ መረኖች መሆናቸውን ማስረጃው የሚፈሰው ደም፣ የሚፈናቀለው ዜጋ፣ የሚሰቀቀው ማኅበረሰብ ምንም የማይመስላቸው መሆኑ ነው።

ብዙኃንን በፕሮፓጋንዳ አቅል አሳጥቶ በእብዶች ሙዚቃ እየደነሱ “ዲሞክራሲ” ነው በሚል ድንዛዜ እውነትንና ፍትሕን የሚገድሉ መሪዎች በዝተዋል። ሙስና ሥራና ጥበብ እንደሆነ የሚያስተምሩና የጥፋት አርአያ የሆኑ የመሥሪያቤት ኃላፊዎች በዘርና በሰፈር ተደራጅተው ጥፋቱን ቀጥለዋል።

በዚህ ጊዜ ከሁሉ በላይ አስቀድማ መቆጣት፣ ማስተማር፣ መምራት የሚገባት የብርሃን ምንጭ ሆና በምድር በክርስቶስ የተተከለችዋ ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያን እና ልጆቿ መሆን ይገባቸዋል። ቤተክርስቲያን

ውግንናዋ ከፓርቲ ፖለቲካ ጋር ሳይሆን ከእውነት፣ ከፍትሕና ከቅድስና ጋር ነውና ምንም ሳታመነታ ስሁት ትምህርትን፣ ማኒፌስቶዎችን፣ የፖለቲካ መርሐግብርና ርእዮቶችን ፈትሻ በአደባባይ መልካሙን መልካም፣ ጥፉውን ውጉዝ ማለት አለባት። ልጆቿን ቡራኬዋንና ውግዘቷን እንደ ማንፀሪያ እየተጠቀሙ የአገራቸውን ፖለቲካ ለቅድስናና ለሰላም፣ለፍቅርና ለአንድነት፣ ለልማትና ሥልጣኔ አንዲያመች አድርገው ይመሩታል፣ ይሳተፉበታል፣ ይገሩታል፣ ይለውጡታል። በዝምታ ካለፈች ግን መልሕቅ አንደሌለው መርከብ በሴኩላር የሀሳብ ገበያ ማዕበል እየተምታቱ ድምጻቸው ይለያያል፣ ሀሳባቸው ኢክርስቲያናዊ በሆኑ ስብከቶች ይከፋፈላልና እና ይዳከማሉ። አገራቸውን ለብልጦችና ለይሉንታ ቢስ የባዕዳን አሽከር ለሆኑ ዘመናዊያን አስረክበው አንግዳ ይሆናሉ። አሁንም ሆነዋል።

ዘሬ ኦርቶዶክሳዊያንን በጎሣ የሚለያዩ፣ አገርን በሰፈር እየሸነሸኑ የሚከፋፈሉና በአንፃሩ የጎሣ ቤተክህነት ለመፍጠር ከፖለቲካው ተጣምረው የሚሠሩ የቤተክህነት ምንደኞችን ያፈራነው፤ የሚያስወርዱና ፅንስ የሚስቀሩ ወላጆች የበዙት፣ ትዳር ከሃይማኖታዊ ምሥጢርና ከመዳን መንገድ ወትቶ በሴኩለር ፍርድ ቤት የሚዳኘው፣ ክርስቲያኖች በሀሰተኛ ትርክት እየተከሰሱ የሚፈናቀሉትና የሚገደሉት ቤተክርስቲያን ልጆቿ በአገራቸው የፖለቲካ ሥርዓትና አቅጣጫ ላይ የጋራ አቋም ይዘው የጋራ አገራቸውን አንዲጠብቁ የሚስችል አስተምህሮ ከማቅረብ በመታቀቧ ነው። ይህ አሁን መለወጥ አለበት።

ክረስቲያኖች የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክር የሚሆኑት ከመናፍቃን በመከራከር፣ ከሀዲያንን ባለመታዘዝ ሰማዕት በመሆን ብቻ ሳይሆን በኑፋቄና በክህደት ፍልስፍና ላይ የተመሠረቱ የፖለቲካ ርእዮቶችን በትምህርትም፣ ተደራጅቶ በአመራጭ የፖለቲካ ርእዮት ሥልጣን በመያዝም ጭምር ነው። ቤተሰብን ክርስቲያናዊ አድርጎ መምራት፣ የትምህርት ሥርዓትና ፖሊሲን ከእምነታችን እሴቶች አንጻር ማቃናት፣ ፍትሕን ከምላስ ወደ ተግባር በማሸጋገር፣ ብዝኃ ባህላነ አምነቶችን በአገራዊ እሴት በማስተጠሳሠርና አንድነት በመፍጠር፣ አገርን ከሁለገብ የምጣኔ ሀብትና የቴክኖሎጂ ጥገኝነት ነፃ በማውጣት ወዘተ ነው። ይህ የሚቻለው አገር ፈለቅ እውቀት፣ ሥርዓትና መዋቅር እየተመራ በሀሳብ ተውሶ ባዕዳንን ከሚያመልኩ የፖለቲካ መሪዎች መገላገል ስንችል ብቻ ነው። ከቅዱስ ሲኖዶስ እስከ አንድ መምሕረ ንሥሐ ድረስ የተዘረጋዊ ክርስቲያናዊ መዋቅራችን የቤት ሥራ ወስዶ አሁን ከምንገኝበት አገር-አልባነት ወደ ባለአገርነት የሚያሸጋግረን ፖለቲካ የምንዘርበትን ንቃት መፍጥር ግድ ሆኗል። ይህ ካልሆን እየለመኑና መንግሥትን እዮስፈቀዱ ማምለክ፣ እየተፈናቀሉ በድንኳን መኖር፣ መሰደድ፣ ተገፍቶ ፍትሕ ማጣት፣ ተገድሎ በጅምላ መቀበር፣ በሐሰት ተከሶ በትምህርት ስም መዋረድ ይቀጥላል። የመንግሥት መዋቅርም የዘረኞችና የሜረኞች፣ ሙሰኞችና ጎጠኞች፣ ብልጦችና ሐሰተኞች የሚገለገሉበት የወንበዴዎች መሣሪያ መሆኑ አይቆምም።

ክርስቲያኖችም በግላችን ለእውነት የምንሞት ነን ብለን ከቅድስት ሥላሴ በጥምቀት መወለዳችንን በማስታወስ በመንፃ ሣጥን ተቆልፎብን ከምንገኘው እሥር ሰብረን በመውጣት በክርስቲያናዊ መሥፈርት ሐሰትን ለመዋጋትና እውነትን ለማጽናት ቁርጥ ሕሊና ማድረግ ይጠበቅብናል። ፀረ-ኦርቶዶክስ ክርስትና

አቋም ያላቸው ግለሰቦችና ፓርቲዎችን ከመከራችን ይገላግሉናል ብለን መጠበቅ የዋኅነት ብቻ ሳይሆን አንድም አላዋቂነት፣ ወይንም የበዛ ፍርኃት፣ ወይንም ከፍተኛ ድንዛዜ ነው። በታሪካችን ለእኛ የቆመና የሠራ፣ ፍትሕ የሰጠን፣ ለእውነት የሚመሰክር መሪ አላጋጠመንም። አንደ አንድ ክርስቲያን እና እንደ ጥሙቃን የሥላሴ ልጆች ማኅበር ከቀሳፊ ፖለቲካ ወደ ፈዋሽ ለሥጋና ለነፍስ የሚጠቅም የፖለቲካ ሥርዓት ለመሸጋገር መጋደል ክርስቲያናዊ ግዴታ እንጂ ትርፍ አይደለም። ለአውነት ከመመስከር ውጭ ለክርስትና ምን ትርጉም ይኖረዋል??

ብዝኃ ባህልና እምነት ባለበት አገር በሃይማኖት የፖለቲካ ሥልጣን መያዝ አይመከረም፣ ለሕዝብ አንድነትና እርካታም አይበጅም። ሃይማኖትና መንግሥታዊ ፖለቲካን በሥልጣን ደረጃ መለያየት ተገቢ ብቻ ሳይሆን ግዴታ ነው። መንግሥትና ቤተክርስቲያን ሁለት የተለያዩ ይህንን መርህ ግን በመለጠጥ ፖለቲካና ሃይማኖት አይገናኙም በሚል ፅንሰ ሀሳብ መለወጥ ፍጹም ክህደት ነው። ሃይማኖትና ባህል የሚመሠረቱበት ማኅበረሰብን እሴት፣ ፍልስፍናና መዋቅር ያጎናፀፉ መንፈሳዊነትና ከምድራዊ አስተዳደር ጋር ያዋሀዱ የአገር ሀብታት ናቸው። እነዚህን ሀብታት ወደ ጎን በመተው በተውሶ የባዕዳን ርዕዮት አገርን ለመምራት መሞከር መልዕክቱ ዜጎችን እሴቶቻችሁን፣ እምነታችሁንና አገር ፈለቅ አውቀታችሁን እስከነ ማሰተገብሪያ መዋቅራቱ አጥፉት ብሎ እንደማወጅ ይቆጠራል። የዚህ አይነት ርእዮት ፀረ-አገር፣ ፀረ-ሃይማኖትና ፀረ-ባህል ነው። ኦርቶዶክሳዊያን ሥራቸው መሆን ያለበት በትምህርትና በአውቀት፣ ሥልጣኑን በመግራትና በመምራት፣ ባለመከፋፈልና በኅበርታዊ አንድነት ማኅቀፍ የሚመራ ርእዮተ ዓለም እንዲሰፍን በመርዳት ብቻ ሳይሆን እስከሞት ለዚህ በመቆም በወንጌል ብርሃናችሁ በሸ ፊጽ ይብራ ያለን አንፈትማለን። ከዚህ ተቃራኒ በመቆም በሰፈርና በቋንቋ፣ በተውሶ ርእዮትና መደብ እያሰብን የኢአማኒን መሣሪያ መሆን ለተጠመቀ ሰው ነውር ብቻ ሳይሆን ኃጢአትም ነው።

በየሰንበቱ የምንሳተፍበት ቅዳሴያችን፣ የምንበላው ሥጋና የምንጠጣው የክርስቶስ ደም በዚህ ምድር በዓለም ሰማያዊነትን አስተባበርን የምንኖር ልዩ ሰዎች መሆናችንን ዘወትር ያሳስበናል፣ እንድንገለጽበትም ኃይል ይሸፀናል። ምፅዐተ ክርስቶስን የምንሰበከውና የምናስቀድሰው፣ ብሎም በጸሎጻችን “ይሕች መንግሥት ያንተ ናትና” የምንለው ወደፊት መሬትና ሰማይ ሲያልፉ ለምንወርሳት ሩቅ መንፈሳዊ ዓለም ብቻ ሳሆን ዛሬም በመንግሥረቱ ለመኖር ያለንን ፈቃድና ልመና ያሳያናል። ይህን መንግሥት በተግባር በአገር አስተዳደር፣ በሕግ፣ በፖሊሲ፣ በርእዮተ ዓለማችን ተቀርፆ ካልተረጎምነው ክርስትና የሀሳብና የሩቅ ቀጠሮ ሃይማኖት ሆኖ ይቀራል። ወይንም ምናባዊና ቅዠታዊ፣ ተግባር አልባ የሰንበት ጫጫታ አድርገነው ኖሮአችንንና አገራችንን በእሕዛባዊና ክህደታዊ ርእዮት በማስመራት ከእግዚአብሔር መንግሥት የራቅን እንሆናለን። ስለዚህ ፖለቲካ ሥራችን ብቻ ሳይሆን ክርስቲያናዊ ሕይወታችን መሆኑን መዘንጋት ራሱን የቻለ ዴኢዝም የተሰኘ የምዕራባዊያን ኑፋቄ ነው።

ዴኢዝም ይህንን ዩኒቨርስ ለሁለት ከፍለው የሚያዩ የምዕራባዊያን ሰዎች የኑፋቄ እምነት ነው። በዚህ እምነት መሠረት ሃይማኖት ራሱን የቻለ የግል ጉዳይ ሲሆን ሕዝብ በሴኩላር ሕይወት እየተመራ የሴኩላር

መንግሥት ማሸንና ግዑዝ አገልጋይ ሆኖ እንዲኖር የሚሰብክ ሀሰተኛ ክርስትና ነው። እኛ ኦርቶዶክሳዊያን በአምሳለ እግዚአብሔር የተፈጠረው የሰው ልጅን የምንረዳው አንድ መንፈሳዊና ሥጋዊ ሕይወት በተዋህዶ ሳይነታጠሉ፣ ተራ ሳይገቡ፣ ቦታና ጊዜ ሳይወሰንላቸው በአንድነት የሚኖር ፍጡር ነው ብለን ነው።

ሰው ከአራቱ ባሕርያተ ሥጋና ከሶስቱ ባሕርያተ ነፍስ ተፈጥሮ በእግዚአብሔር የሕይወት እስትንፋስ እፍ የተባለበት ፍጡር መሁኑ የሚነግረን ነገር ሰው ሥን ፍጥረት ሁሉ የተጠቃለለበትና በተጨማረ በእግዚአብሔር እስንፋስ የከበረ፣ በክርስቶስ ሰው መሆን ፍጹም የአባቱን መንግሥት የሚወርስ ባለሥልጣንና ልጅ መሆኑን እንረዳለን። ስለዚህ ሰው ሲፈጠር የሚታየውንና የማይታየው የተወሐዱበት፣ ሌሎች ጥረታት ሁሉ እርሱን ለማገልገል፣ እርሱም ፍጥረታትን ሊጠብቅ፣ ሊያበጅ፣ ሊቀድስ፣ ለአምልኩ መልሶ ሊሰዋ፣ ሊኖርበት፣ አምልኮቱን ሊገልጽበት የተሰጡት ናቸው። ይህን ባለቤትነትና አገልግሎትና ለመግለጽ ቦታ፣ ጊዜ፣ እውቀት፣ ሥርዓት፣ ክሂሎት፣ አቅም፣ አስተዳደር፣ ሕግ ማንነት ያስፈልጋዋል። ተሰጥቶታልም። ጊዜ ከቁጥጥሩ ውጭ ሆና እየሄደችም እየዐወደችም ትጓዛለች፣ ቦታ አገር ተሰጥቶታል፣ በአገሩ የሚታረስበት፣ የሚደቀስበት፣ የሚድርበት ተረክቧል። ለመቀደስ ክህነትን፣ ለማስተዳደር ንግሥናን፣ ለሥርዓትና ለአምልኮ ሕግና እውቀትን አግኝቷል። በእነዚህ ፀጋዎች የሚታየውንና የማይታየውን ዓለም አዋህዶ መኖር የሚገባው ልዩ ፍጡር ነው ብለን እንደምናምን ይታወቃል። ይህንን እምነታችንን በተግባር ለመኖር ከፈለግን አገር፣ ቦታ፣ ጊዜ፣ ሕግ፣ እውቀትና ክሂሎት፣ መቀደስና መጠበቅ ኃላፊነት ሆኖ በትከሻችን ላይ የወደቀ ነው። ይህ ሸክም በአገር አስተዳደር ደረጃ ሲገለጽ ፖለቲካ ነው። ስለዚህ ክርስቲያን ፖለቲካ አይመለከተኝም ካለ በራሱ ስህትተ ብቻ ሳይሆን ኑፋቄ ነው። ከኑፋቄም አልፎ ንግሥናን፣ ክሕነታችንን፣ ፍጥረት ሁሉ በእኛ መጠቃለሉን መካድና በሌሎች ድካም ለመኖር የሚደረግ ክህደትም ነው።

ለኦርቶዶክሳዊያን ፖለቲካችብ ንጥልና ግንጥል ሆኖ የሚመለከትንና የማይመለከት በሚልአይከፈለም። ዳኝነቱ፣ መዋቅሩ፣ ፖሊሲው፣ የሀብት አጠቃቀሙ በአጠቃላይ የቁሳዊው ዓለም አስተዳደርና አገልግሎቱ ለመንፈሳዊው ዓለም የተገዛ መሆን አለበት። የዓለም ቁስ ሀብታት አጠቃቀማቸውና አስተዳደራቸው ጠቃሚነትና ጎጅነት የሚመዘነው በነፍስ ሚዛን ሆኖ ሥጋ ማስፈጸሚያው ነው። የፖለቲካ አይነት ትቅምና ጉዳት በሆድ ሙሌት፣ በሥጋ ጌጥ፣ በስነ ልቡና እርካታና በነጽጽራዊ ብልጫ የሚለካ አይደለም። መንፈስንና ቁስን፣ ሰማይና ምድርን፣ ሰውና መላዕክትን፣ ፈጣሪና ጡራኑን የሚያገናኝ ተደርጎ መሠፈር አለበት።

ዛሬ ያለው የኢትዮጵያ ፖለቲካ ግን ሊነግረን የሚፈልገው፡-

- ስለ ምግብ፣ ትራስፖረት፣ ጤና፣ የአገር ገጽታ፣ ወዘት “ልማት” (የልማት ትርጉሙ በቁስ ብቻ ተመዝኖ፣ ሞራል፣ መንፈሳዊነትን፣ ፍቅርና ሰላምን ዋጋ አሳትቶ)
- በሕይወት የሌሉ የቀደሙ ሕዝቦችን ታሪካዊ በደሎች (ለዚያውም በሀሰት ተፈብርኮ) እርማትን በሕይወት በሚኖሩት ሰዎች የህይወት ዋጋ ተበደሉ ለተባሉት (በሌለበት) ዘመን ውስጠ የማካካስ በቀል፣

- ስለ ልዩ ማንነቶች ልዩ መብቶች (ሰው ከሰው፣ ዜጋ ከዜጋ ተበላልጦ ለአንዱ ልዩ ጥቅም ለሌላው ልዩ መከራ)፣ መዝናኛ (ሕሊና እግዚአብሔርን የምንዘነጋበት) ብቻ ነው።

ይህንን የፖለቲካ ፅንሰ አሳብ የወለደው የምዕራባዊያን የኑፋቄና የክህደት ፍልስፍና ተጎዳኝነት ነው። ፖለቲካችንም የሚካሄደው በመዋስ ስለሆነ አገራዊ የመኖር ትርጉምን የማዳከም መንገድ የሚመርጥ አገር-በቀል ሀብታትን በመጥላጥና በማትፋት ላይ ያተኩራል። እግሮች የሚፈቱት አገራዊነት ሲጠፋ መስለዋል። በዚህ አንፃር አገርን ሠራችዋ ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያንና ኦርቶዶክሳዊ ሰው እንደዜጋ በአገሩ ጉዳይ የማይሳተፍበት መንገድ ሁሉ ተመቻችቶ ይሠራበታል። ፖሊሲዎችን ሕጎች ሁሉ ታሪክን የሚከሱ፣ ኦርቶዶክስን የሚያረክሱ፣ መሪዎቻን የሚዋርዱና የሚገልሉ፣ ዛሬ ደግሞ ልጆቿን የሚስገድሉ ሆነዋል።

የለውጥ ታሪካችን ሁሉ በተውሶ ጀምሮ በቁልቁሊት ውድቀት የሚጠናቀቅ ነው። የ1966ቱ ተማሪ ቅስቀሳ ሀሳቡን የተዋሰው ከባዕዳን ኮሚኒስቶች ነበር። ስብከቱ ለሁሉም እንደየ ፍላጎቱ፣ ለእያንዳዱ እንደችሎታው ይሰጠዋል የሚልነው። ቁሳዊ ሀብትን እኩል እንዳታገኝ እንቅፋት የሆነብህ ዘውዳዊ አስተዳደር ነው፤ ዘውድን እውቅና የምትሰጠው የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ናት በሚል ተስፋ ያስደረገውን ውጤት ለማስገኘት ሁለቱ መጥፋት አለባቸው ብሎ ይበይናል። ተስፈኛ መንጋ አስከትሎ አገራዊነትን ድምስሷል። እኩልነትን ለማምጣት ንጉሡን መግደል፣ ጳጳሱን ማነቅ፣ አስቀድሞ የነበረውን እውቀትና አስተሳሰብ ማንኪሰስ፣ አዋቂዎቹን በተለይ 66ቱን ምሁራን ገድሎ በአንድ ጉድጓድ መቅበር፣ ቀጥሎ በአንጃ ተከፋፍሎ መጨራረስ ላይ ተሰማራ። የመጨራረሱ መንገድ የዘቀጠው ሄዶ ወደ ጎሳና ዝር ፖለቲካ ደረሰ። ይህ ፖለቲካ ዘውግ እያበጀ ነፃ አውጭ በመሆን አልጠገብ ባይ የሀብትና የመንደላቀቅ ኑሮውን በፖለቲካ ሥልጣን በኩል ለመወጣት ሌቦችን ወደ አገር አመራር አደረሰ። ውጤቱ ግን ከድንግዝግዝ ወደ ድቅድቅ ጨለማ መጓዝ ነበር። ዛሬ የቆምነው ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ሆነን ያንኑ በ1960ዎቹ መብራታችንን ያጠፋውን ትራፊ ትውልድ መፍትሔ ስጡን ብለን እንጠብቃለን። እንከተላለን። በትግራይ ነጻ አውጭ ዘረንነት ሕገ መንግሥት ሆኖ በዚያው ሕግ ፓርቲው ጦርነት ውስጥ ገብቶ መቃብር ጫፍ ቆሟል፤ እርሱን ለመቅበር አካፋ ዘው የቆሙት የዛሬ ባለሥልጣናትም ገና ሟቹን ሳቀብሩ የሚቀብሩት አጥፊ ያዘጋጀውን ሕገ መንግሥትና ዘረኝንት የፖለቲካ ሥርዓት አድርገው ኦርቶዶክስን ከአካባቢያቸው ለማጽዳት ይሠራሉ፤ ሥልጣን በጎሣ ይደለድላሉ፣ የገርን ክፍለ-አስተዳደሮች ልክ እንደሉዓለዊ አገር ይሕ የእኔ ብቻ ነው፣ ያኛው ያንተ ነው በሚልፖለቲካ ይራኮታሉ፤ ያፈናቅላሉ፣ ሥልጣን ይደለድላሉ፣ ሀብት ያሻማሉ። ይህ ሂደት ብሩሕ ተስፋን ሳይሆን ድቅድ ጨለማን ያመለክታል። ---- ስለዚህ አዲሱ ትውልድ አዲስ የተውሶ ያይደለ ኢትዮጵያዊ አስተሳሰብን ተመርኩዞ ራሱን ነፃ ማውጣት አለበት።

ኦርቶዶክሳዊያን ሆይ!

በቅዳሴአችን ምእመን ያመጣውን ስንዴ እና ወይን በእግዚአብሔር ፈቃድ እና ተአምራት፣ በክሕነት በኩል ወደ ሰማያዊ ምግብ በመለወጥ እየተዳሰሰ እና እየተቀመሰ ተቀብለን ከሰውነታችን ጋር የምናዋኅደው የክርስቶስ መለኮት የተዋሐደው ሥጋ እና ደም ሰማያዊያን እንደምንሆን እናውቃለን። ይህን ሰማና ምድርን፣መንፈስና ቁስን፣ ሰውነትንና መልዐክነትን፣ ርቀትና ግዘፍን ያዋሓደ ሕይወት የምንመራ እኛ

ኦርቶዶክሳዊያን ፖለቲካና ሃይማኖት ይለያያል በሚሉ የምዕረባዊያን የዴኢስቶች ትምህርት ተታለን ቁሳዊውን ነገር ሁሉ እግዚአብሔርን እንደ አምላክነቱ ላልተረዱት መናፍቃን፣ የለም ላሉት ከሀዲያን፣ የእግዚአብሔርን ባሕርያቱን ለውጠው በመላምታዊ አስተምህሮ የራሳቸውን አምልኮ ለፈጠሩ ስሁታን ትተንላቸው ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ ኖርን። አገራችንን ማለትም ግማሽ ማንነታችንን የቁስ አምላኪ ሴኩላሪስቶች አስረክበን ፖለቲካ አይመለከተንም በሚል ጨለማ ውስጥ የጨለማ መንገደኞችን እንከተላለን። እናንተ የዓለም ብርሓን እና ጨው ናችሁ ያለንን ዓምላካዊ ትምህርት ዘንግተን ግለሰቦችና ፓርቲዎችን አንዲያበሩልን እንጠብቃለን። ጨለማ በራሱ ጨለማ ነውና ለጨለማ መወገድ ምክኒያት ሊሆን አይችልም።

እኛ ብርሃን የብርሃናዊ ኢየሰሱ ክርስቶስ ልጆች ነን። በቅዱስ ቁርባን ሁሉን የምናዋህድ እኛ ፖለቲካን በሃማኖት ማያ መፈወስ እንደሚጠበቅብን ለብዙ ዘመናት ዘንግተን ኖርን። በዚህ ዝንጋኤ ምክኒያት የጨለማልጆች ያርዱናል፣ በፖለቲካ ስም ያሳድዱናል፣ ያገዳድሉናል፣ በጅምላ ቀብሩናል፣ ለልማትና ለሥልጣኔ አትሆኑ ብለው እንድንጠፋ በሠራናት አገር ባይተዋር ያድረጉናል።

የሰው መዳን ሀሳባዊ አይደለም። የሰንበት ዕለት ብቻ መንፈሳዊ የአምልኮ ሥርዓት ብቻም አይደለም። ክርስትና ምንታዌ (ሁለትነት) አይስማማትም። አምልኮም ኑሮም አይነጣጠሉባትም። የኦቶዶክስ ክርስትና ተግባራዊ ሕይወት መሆኑን በተጨባጭ የምንረዳው በአምላክ ሰው መሆን፣ መሰደድ፣ መሞትና ትንሳዔ ነው። የማይጨበጥ አምላክ በሥጋ ማሪያም የተጨበጠው በዚህ መድር ባሉ ስብስቦች ነው፣ ፍርድ የተፈረደበት በዘመኑ በነበረው የፖለቲካ ባለሥልጣን ነው፣ ፍርዱ የሚፈጸምበት መስቀል የተተከለው በዚሁ የመንግሥት አስተዳደር ባለበት አገር በቁሳዊው ምድር ላይ ነው፣ ደሙም የፈሰሰው በዚሁ መሬት ላይ ሲሆን አስፋሽቹም በመንግሥት የሚተዳደሩ ሰዎች ናቸው፣ ጌታ የተቀበረው በአንድ አይሁዳዊ መቃብር በመሪት ላይ ነው፣ ትንሳዔውን ያበሰረው እዚሁ በፖለቲካ በሚተዳደር የእሥራኤል ምድር ነው፣ “ይህ መንግሠት ትሰጠን ዘሬ በሉ፣ የአግዚአብሔር መንግሥት በመጠባበቅ አትመጣም፣ በመካከላችሁ ናት” ብሎ ያስተማረው በታወቀ አገር ውስጥ በፖለቲካ ሥርዓት ለሚመሩ ተከታዮቹ ነው፣ የገንዘብ ግብርን ለቄሣር ከፍሎ የእግዚአብሔር ገንዘብ የሆነው የሰው ልጅ ግን ለእግዚበእሔር እንደሆነ አንዲኖር የቁሣርን ለቄሣር፣ የአግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር” ብሎ ሁለትነትን አጠፋ። እንግዲህ ሁሉን ሳንከፍል፣ ሳናጋጭ፣ ሳንለያይ አዋህደን የምናምን እና በተግባር ልንመሰክር መስቀል የምንሸከም እኛ ኦርቶዶክሳዊያን ሃይማኖታችንን የምንገለፅበት የሕይወት ተግባራትን በሚወስነው ፖለቲካ ሳንሳተፍ አምልኮን መፈተም እንዴት እንችላለን? ቅዳሴ እኮ የምደሩን ሰማያዊ፣ የሰማዩን ወደ ምድር ጠርቶ የማዋሐድ በዚህ ዓለም ሰማያዊያን የምንሆንበት ነው። የቤተመቅደሱን ቅዳሴ ለብሰን በዓለም በሕይወት ዙሪያችን የምንቀድስብት ቦታ፣ጊዜ፣ ሕግ፣ ሥርዓትና ሕዝባዊ መስተጋብር ያስፈልገናል። ይህ ፍላጎት ፖለቲካዊ ፍላጎት ነው።

ከፖለቲካ ውጭ ለመሆን መሞከር በራሱ በሥጋም በነፍስም የሚገድል መሆኑን ዛሬ የሚደርስብን ማቆሚያ ያጣው ግፍ በተግባር አስተምሮናል። በሥጋው በግፍ ከሚገደለው የበለጠ በፍርሃትና ተስፋ በመቁረጥ ከሃይማኖት የሚወጣው ይበዛል። ሁለቱም ሞቶች እኛ የሌለንበት ያልተቀደሰ ፖለቲካ ውጤቶች ናቸው።

ሁሉን የምታዋሕድ እምነት እየተከተሉ፣ የመንፈሳዊና ቁሳዊ ዓለም ፈጣሪና ገዥ የሆነ የንጉሥ ክርስቶስ ልጅ ሆነው እያሉ "ፖለቲካ አይመለከተኝም ማለት" ቅዠትም ክህደትም ካልሆን ምን ሊሆን ይችላል?

ድንዛዜና ኑፋቄያችን እዚህ ላይ ያብቃ!!! አገራችንን ለእኛ እንደሆነች የሚያረጋግጥ ሕግ፣ፖሊሲ፣ መዋቅር፣ ማኅበራዊ መስተጋብር፣ ትምህረት፣ ኪነ ጥበብ ማንበር ያስፈልጋል።

ቤተክርስቲያንን መንግሥት

የቤተክርስቲያንና መንግሥት ግኑኝነት ውስብስብ ሆኖ የሚታየው ክርስቲያኖች ለሴኩላሪስቶች ዓለምን አስረክበው ማሰብ ከጀመሩ በኃላ ነው። በታሪካችን ያለን ልምድ ቤተክርስቲያን በዋሻ ውስጥ በሰማዕተነት፣ በስደትና በመካራ ኖራለች፤ በተቀደሰ ንጉሥ በቁስጢንጢኖስ ታዛዥነትና እውቅና መሥጠት፣ በእግዚአብሔር ተአምራትና ገላጭነት በቤተ መንግሥት እያዘዘችም ኖራለች፤ ነገሥታትን እየቀባጭ ነፍሳትን የመጠበቅ ተልዕኮዋ አካል አድርጋ ምድራዊ መንግሥትን ለሰማዊ መንግሥት አስገዝታለች።

ዛሬ ግን ያኃጠማነት አዲስ ነገር ነው። ወደ ዋሻም አትገባ፣ ወደ ቤተመንግሥትም አትደርስ--- እንዳው በፍዘትና በመጭበርበር ልጆቿን ለተኩላ የሰጠች ትመስላለች። የቄሳርን ለቄሳር የአግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር እየሰጠው ልኑር ስትል፣ የለም ሁሉም እኛ በገባንና በፈቀድነው መጠን ይሁን የሚሉ በክህደትና በእምነት መካከል ቆመው ግራ የሚያጋቡ አጭበርባሪዎች አስቸግረዋታል። የቄሣርንም የእግዚአብሔርንም ወስደነዋል፤ አንቺ ቅርሥ ነሽ፣ የድሮ ቆንጆ መዝናኛ ነሽ፣ የሚያምርብሽ መጎብኘትና መታየት አንጂ መምራት ኤመለከትሽም ተብላለች። እናውቃለን! ክርስቶስ ሥርዓተ መንግሥትን በፖለቲካዊ ርእዮት የመሠረተ ንጉሥ አይደለም፤ አርሱ የሥርዓት ሁሉ ፍጻሜ፣ የአስተዳደር ሁሉ መሠረት፣ የነግሥታት ንጉሥ ነውና የመዳን መንገድን አዋጅ ብቻ ሰጥቶን ሰው ሁሉ በነፃ ፈቃዱ ተመርቶ እንዲኖርበት አሳየ እንጂ።

ጌታችን ስለ ትዕዛዝም ሲነግረን ለእርሱ እና እርሱ ለፈቀደለት ሰብአዊ መንግሥት እንደታዘዝ ዘንድ ነው። መታዘዝ ግን ገደብ አለው፤ ገደቡም አምልኮተ እግዚአብሔርን የሚከለክል፣ አገር አልባ፣ መቅደስ አፍራሽ፣ ጣዖት ዘርን አስመላኪ፣ ኑፋቄ ዘሪ፣ የክህደት አስተማሪን ሁሉ በነፍሳችን ተወራርደን እንድንቃወም በሮም አደባባይ ምሳሌ በሆኑን ቅዱሳን ሓዋሪያት ጳውሎስና ጴጥሮስ ሰማትነት፣ ለቁጥር ስፍር በሚያታክቱ አያሌ ሰማዕታት አርአያነት ነግሮናል። በዚህ ለቄሣር ስንታዘዝ ለእግዚብሔር መታዘዝን ትተንና ዘንግተን፣ ወይንም ቅደም ተከተልና ተራ አውጥተንለት እንዳልሆነ አሳውቆናል። በሰንበት ዕለት በቅድረ ቤተክርስቲያን በእግዚአብሔር ካህናት ስንገለገልና ስናገለግል ውለን ቀሪውን 6ቱን ቀናት ግን ከእግዚአብሔር ሕግና አሠራር ውጭ ሊነዱን ቆርጠው ለሚፈልጉ የፖለቲካ ርዕዮተዓለማትና ሕግጋት ሁሉ በመሣሪያነት እንድናገለግል አልታዘዝንም። በተቃራኒው ነው የታዘዝነው። ክርስቲያኖች በሁሉ ቦታ፣ በሁሉ ሁኔታና በሁሉ ጊዜ "እኔን መስላችሁ አብሩ" አለን እንጂ።

ዘመንና ቦታ፣ ሁኔታና የፖለቲካ ርእዮትን፣ የመንግሥት ቅርጽን ተከትለን እንድንለዋወጥ አልተፈቀደልንም። ብርሃን ከማብራትና ጨለማን ከማስወገድ የተለየ ማንነት ሊኖረው ኤችልም፤ ጨው ሌላውን ከማጣፈጥ የተለየ ግብር የለውም። ክርስቲያኖችም ብርሃንና ጨው ሆነው አልጫውን ፖለቲካ ከማጣፈት፣የጨለማ ርዕዮቶችን ከማስወገድ የተለየ ሥራ በዚህ ምድር በዓለም የላቸውም። ጌታችን ስለ ዘውድ፣ ስለ ኮሚኒዝም፣ ስለ ሊብራል፣ ስለ ማንነት ወዘተ ፖለቲካ አልነገረንም። በመልክዐ ምድራዊ ወሰን ውስጥ ሰብአዊ የፖለቲካ ርዕዮትን በመታዘዝ አምልኮተ እግዚአብሔርን በተግባራዊ ሕይወት እንዳንገልፀው የሚያደናቅፈንን ሁኔታ ሁሉ መስቀሌን በመሸከም ድል ትነሱት ዘነድ ጲላጦስንም፣ የአይሁድንም ጫጫታ እስከሞት የተቃወምኩትንና እውነትን በመስቀል ሞት የተውኩላችሁን እኔን ምሰሌ ነው ያለን። እርሱን ጌታችን ራሱም ሆነ ተከታዮቹ ሐዋሪያት የሚያስተምሩትን በመቃረን ሰውን ከእግዚአብሔር አስተምህሮ ወደ ስህተት ለመምራት የሞከሩትን የሮማ ነገሥታት ተቃውመው ሰማዕትነትን ተቀብለው አልፈዋል።

ቤተክርስቲያን ራሷ የሥርዓት ቤት ስለሆነች ሥርዓትን የሚያስከብር፣ ሰላምን የሚያሰፍን መንግሥት ትደግፋለች፣ ታበረታታለች፣ ተከታዮቿም መንግሥትን እንዲታዘዙ ትመክራለች። መታዘዝና መተዳደር ግን ከሕገ እግዚአብሔር በታች መሆናቸውን ታፀናለች። በዚህም አንድን ሰብአዊ የፖለቲካ ርእዮት እየመረጠች የምትደግፍ እና ሌላውን የምትቃወም መሆን አትችልም። የእርሷ የማይለዋወጥ አቋም ፖለቲካና ሕግጋቶች ሰዎችን ከእግዚአብሔር በሚለይ መንገድ የሚሰበክ፣ የሚዋቀርና የሚመራ ከሆነ ብቻ ነው። በተረፈ ልጆቿ ሕገ እግዚአብሔርንና የአጠቃላይ የማኅበረ ክርስቲያንን መንፈሳዊና ሥጋዊ ጠቀሜታ ታሳቢ በማድረግ በክርስቲያናዊ መሥፈርት እና ስሌት ፓርቲ ሊፈጥሩ፣ ሊደግፉ፣ ሊቃወሙና ሊመሩ ይችላሉ ብቻ ሳይሆን በእገዚአብሔር ሕግ ልኬትነት እስከሆነ ድረስ በአገራቸው መምራት ግዴታቸውም ነው።

ክርስቲያኖችና ምርጫ

እንደ ቅዱሳን ነግሥታት ዘመን ካህናት ነግሠውና አስተዳዳሪ ሆነው የፖለቲካ ተቋምን የሚመሩበት ዘመን የኢትዮጵያ የኖር የቅድስና ዘመን መገለጫ ነው። እንደ ይምርሓነ ክርስቶስና ላሊበላ የዚህ ምሳሌ ናቸው። በዚያን ዘመን አገር በአብዛኛው ክርስቲያን ነበር፣ አረባዊያን አልወረሯትም፣ መናፍቃን አልሰረጉባትም፣ ኮሚኒስቶችና ሴኩላሪስቶች አልናኙባትም። አሁን ግን አገሪቷ ከኖኅ ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ሰማያዊ ስነ መንግሥት አጥታለች፣ በኃያላን አገራት ፍላጎትና አስተምህሮ የምትመራበት ዘመን ነው። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ክርስቲያኖች አገርን እንደ አገራቸው ለመምራትና ለመመራት ሕገ እግዚአብሔርን የሚያስከብር ሥርዓተ-መንግሥት ለማቆም የመደራደር ግዴታ ውስጥ እንገኛለን። በአገራችን ከእኛ ከዜጎች የማይመነጭ፣ በሩቅ ጠላተቻችን የተጫነብን እርሱ በእርሱ የሚጋጭ ፍላጎቶች አዳብረናል። በተለያዩ ፖለቲካዊ ፍልስፍናዎችና ፍላጎቶች መካከል ቆመን አንድን የጋራ አገር የማስተዳደርና ለሁሉም እንደ ሰውና እንደዜጋ ተከብሮና አክብሮ፣ ግዴታውን ተወጥቶና መብቱን አስጠብቆ የሚኖረበት ሠርዓተ መንግሥት ማንበር የተወሳሰብ ሥራ ሆኖ ቀርቦልናል።

አገራችንን የሚያስተዳድሩ፣ለማስተዳደር በየፖለቲካው ድርጅት ተሰባስበው የሚጠባበቁ ሁሉ የእኛን የኦርቶዶክሳዊያንን ክርስቲያናዊ ፍላጎቶች፣ መብቶችና ፍልስፍናዎች የሚቃረኑ ሆነው ለትፋታችን ደፋ ቀና የሚሉ ሆነው ተገኝተዋል። የቤተክርስቲያን ፍላጎት ግልፅ ነው። እርሱም የመንግሥት ሥልጣን ይዘው አገሪቷን የሚስተዳድሪ አካላት ሕግ፣ ፖሊሲ፣ ትምህርት፣ የልማትና የሥልጣኔ ትልምና አካሄድ ሁሉ የኦርቶዶክሳዊያንን በአሰተምህሮአውና በእምነታው ምክኒያት ሊኖሩት የሚሹትን አይነት ሕይወት የሚገዳደርና በረዥም ሂደት የሚያዳክም የጠላት አጀንዳ መስሎ መቅረቡ እንዳይቀጥል ነው። ክርስቲያኖች በእምነታቸውና የፖለቲካ ርእዮታቸውን አስማምተው መኖር ይፈልጋሉ፣ ግዴታቸውም ነው። ይህን ግዴታ እንዳይወጡ በተውሶ ውጭ-ገብ የፖለቲካ ፍልስፍና አንፃር በአዲስ መንገድ እንድትተዳደርና እንድንለወጥ የሚፈልጉትን የፖለቲካ ፓርቲዎች ፈጽማ መቃወም፣ ልጆቿ እንዲዋጉት ማስተማር የተልዕኮዋ አካል ነው። በዚህ ምክኒያት ግጭት ይኖራል። አነዚህን ግጭቶች ከግንዛቤ ያስገባ፣ የሌሎች እምነቶችና ባህሎችን የዜግነት መብቶች ያገናዘበ ማዕከላዊ መንገድ እንዲኖር ክርስቲያኖች በንቃት ፖለቲካውን መምራት ይጠበቅባቸዋል።

እስከአሁን በምናየው የፖለቲካ ሂደት ክርስቲያኖች በመምረጥና በመመረጥ ሂደት የነበራቸው ተሳትፎ ኦርቶዶክሳዊ ፍላጎትን ያላገናዘበ እና ከክርስትና እጅግ ባነሱ ንዑሳን ማንነቶች በሚመሬ የፖለቲካ ቡድኖች ዙሪያ ተኮልኩለውና ተበታትነው ነበር። ኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያናዊ ፍላጎትን ማዕከል አድርገው በአንድነት ቆመው አያውቁም። ዘረኞችና ጎሠኞች ተከፋፍለዋቸው እንደ ልቅሶ ቤት ንፌሮ በየበኩላቸው አንዲያፍሷቸውና ለፈለጉት ግብ እንዲጠቀሙባቸው ሆነዋል። ይህ ሂደት ክርስቲያኖችን በአገራቸው አንግዳ፣ ለፖለቲካው ባዕድ አድርጎ በጅምላ እሰከመጨፍጨፍና መሰደድ ዳርጓቸዋል። በፖለቲካው በንቃት መሳተፍ የደረሰብን ግፍ በቂ ልምድ ስለሰጠን ከአሁን በኃላ የክርስቲያኖች ዋና ትኩረታቸው አገራዊ ሁለገብ ተሳትፎና መምራት ላይ መሆን ይኖርበታል። የአገር ባለቤት ሳሆኑ ግብር መክፈል፣ በየጦርነቱን አገርን ለመጠበቅ ደም ማፍሰስና አጥንት መከስከስ ብቻውን የአገር ባለቤት አያሰኝም። ሳይመረጡና ሳመርጡ በሚመሠረት መንግሥት ሥር ፀረ-ኦርቶዶክስ ርእዮተ ዓለም፣ የመደበኟ ትምህርት ይዘት፣ ሕግና ፖሊሲ መስፈኑና ባለፉት 50 ዘመናት እንደታየው ስደትና ሞት ሊያጋጥመን ይችላል። የሚሞቱላትን፣ የሚፀልዩላትን፣ የሚለሟትን አገር ማስተዳደር የዜጎች ሁሉ እኩል ድርሻ አላን። እየተገደልን፣ እየተገለልን ግዴታን ብቻ ለመወጣት መታዘዝ ከሰውንት ማነስ፣ ታሪክን መዋረድ፣ ፍጥረታችንን መዋረድ፣ በምድር የተሠጠንን ብርሃን የመሆን ተልዕኮነዘንጋት ነው።

ቤተክርስቲያን ከዚህ ዓለም ያልሆን ነገር ግን በዚህ ዓለም እየኖረች ለሰማያዊ ግብ የምትሠራ ናትና ፖለቲካዋ ይህን ያገናዘበ ነው። ምድርና የምድርን፣ ሆድና አካልን ብቻ የሚስቡ ሰዎች የሚመሩት ፖለቲካና አስተዳደር ለክርስቲያኖች ጠላት ሆኖ እንደሚነሳ አገራችን የለፈችባቸው አብዮቶችና የአመፀኞች አስተዳደር ገልፆልናል። ክርስቲያኖች ሁሉ መነኮሳትና ገዳማዊያን አይደሉም። በዚህ ዓለም ነግደው፣ አርሰው፣

ተፈላስፈው፣ ዓለም አቀፍ ግኑንነት መሥርተው፣ ዓለም አቀፍ ጦርነት ተዋግተው፣ አገር መርተውና ተመርተው የሚኖሩ በመሆናቸው የፖለቲካ ሥርዓቱ ክርስቲያናዊ ማንነታቸውን የሚደግፍ ሆኖ መሠራት ይኖርበታል። ዛሬ የምናየው ኦርቶዶክሶች ለልማትና ለብልፅግና ስለማስማሙ፣ በቀደመው ዘመን ጨቋኞች መሠሪያ ስለነበራችሁ፣ የነፍጠኛ እምነት በግድ በሌላው ጎሣ ላይ ስለጫናችሁ ዛሬ ላጥፋችሁ የሚል ከባዕዳን በተውሶ የመጣ የፖለቲካ ርእዮት በተጨባጭ አለ። ይህን አውነታ እያዩ እንዳላዩ፣ ሳያርሙትና ሳያርቁት የሚያልፉ ክርስቲያኖች ለቤተክርስቲያን መትፋት፣ ለኢትዮጵያ ከዓለም ካርታ መደለዝ ተጠያቂ ይሆናሉ። ፀረ-ክርስትና አቋም ያላቸው የፖለቲካ ልሒቃን አገራችንን ለመመምራት በምርጫ ስም ሕጋዊ አንዲሆኑ መፍቀድ በራሱ ክህደት ነውና በንቃት አገራችንን በሁለገብ ዘርፎች ሁሉ እንጠብቃት።

ማንን እንምረጥ?

ኦርቶዶክሳዊያን ስለ ምርጫ ሲያስቡ የቀረበላቸውን ድርጅት ቅርጽና ምላስ ሳይሆን እምነትና ፍልስፍና፣ ርዕዮትና እሴት ሁሉ በመመዘን መሆን ይገባል። በዚህ ዘመን ፖለቲካው በጎሣ የተደራጀ፣ ታሪክና ቀዳሚ እውቀቶችን የሚጠላ፣ ለባዕዳን የተገዛ፣ ከሁሉ በላይ ኦርቶዶክሳዊያንን የማዳከም ግብ ያለው ሆኖ ስለሚታይ የክርስቲያን የምርጫ መስፍርት ልዩ ጥንቃቄ ይፈልጋል። እስከዚህ መገፋት ያደረሰንን ሂደት ለማስታወስ ያህል ይህን ሠንጠረዥ እናጡነው፡-



የኦርቶዶክስ አስተምህሮ የሰዎችን መልካም ስነ ምግባር፣ አንድነት፣ ቅድስና፣ ትሥሥርና መረዳዳት ከድኅነት ጋር አያይዞ የሚያሳይ ሰማያዊውን ዓላማ ለምድራዊው ስማማ ነው። የምርጫ መሥፍርታችንም ይኼንኑ ታሳቢ ያደረገ መሆን ይገባዋል። ድልድይ፣ ግድብ፣ ወደብ፣ እርሻ፣ ንገድ፣ ገቢ፣ ሥራ፣ በምት፣ ነፃነት ወዘተ የተሰኙ በምርቻ ወቅት የሚነገሩ ፅንሰ ሀሳቦች ክርስቲያናዊ መሥፍርቶችን እንዳሸፍኑ በግልጽ መማማርና የጋራ ክርስቲያናዊ ድምዳሜ ላይ መድረስ ያስፈልጋል። እነዚህ ቁሳዊ የተመራጭ መለኪያዎች የማንናውም መንግሥት ግዴታዎች እንጂ ክርስቲያናዊ ፍላጎቶቻችንን አንድነዘነጋ ምክኒያት የሚሆኑ አይደሉም።

የዚህ ዓመት ምርጫ አንገብጋቢ መሥፍርቶች

በአሁኑ ጊዜ ተንቀናል፣ ተዋርደናል፣ ተሰድበናል፣ በሀሰት ተከሰናል፣ ተፈናቅለናል፣ ተገድለናል፣ ከፖለቲካ ሥልጣን ተገልለናል፣ ሃይማኖታችንን ለጎሣ መድበው የሚሳድዱን በዝተዋል፣ ፍትሕ ተነፍጋል። ከዚህ በመነሳት ይህን ግፍ የሚዮስቆም፣ ፍትሕና እኩልነትና በጎሣና በቋንቋ እየከፈለ የሚያድል ፖለቲካን ፈጽሞ የምንገድብበት መንገድ ላይ ማቶኮር ይኖርብናል። ስለዚህ ኦርቶዶክሳዊያን ፖለቲካን በሚመለከት መመሪያ ማድረግ የሚገባቸው መንፈሳዊና ሥጋዊውን የሰው ልጅ ማንነት ሳይሸራርፍና ሳያጣምም የመተዳደር፣ የመምራትና የመመራት መርህዎችን ነው።

እኛ ኦርቶዶክሳዊያን የፖለቲካ ማንነታችን የሚቆምባቸው አራት ምሰሶዎች አሉ። በእነዚህ ምሰሶዎች አንፃር የማንደራደርባቸው ፍላጎቶች አሉን። ምሶሶዎቹ

(1) **ሰውነት፡-** (በእግዚአብሔር አምሳልና አርአያ በመፈጠራችን የተሰጠን ሰብአዊ ክብር)
(2) **ሁሉን-አቀፍ የአስተዳደርና የፍትሕ ሥርዓት፡-** ሁሉን አዋህዶ የሚረዳ፣ የሚመኝና የሚያደርግ ኦርቶዶክሳዊ ክርሰትና (ቁሳዊና መንፈሳዊ፣ ሥጋዊና ነፍሳዊ፣ ሳነጥሉ ባለቤት ሆኖ ማስተዳደር)
(3) **የኢትዮጵያ ዜጋዊነት፡-** ብዝኃ-እምነጽ፣ብዝኃ-ባኅህል፣ ብዝኃ-አሠፋፈርን በእግዚአብሔር አምሳል ማስተዳደርና ማደር
(4) **የማይነጣጠሉ ባለሁለት ርስት ባለቤትነት፡-** በምድር የአገር ባለቤት፣ ለሰማዊ ርስት ወራሽነት የምድራዊ ርስት በቤተመቅደስነት የማገልገል ድርሻና

እግዚእአብሔር ፍጥረታትን ሁሉ ለሰው ልጅ ሥጋዊ ጥቅም እና መንፈሳዊ ሕያውነት መሆኑን፣ ሰውም በአግዚእብሔር አምሳል በፍጥረት ላይ የነገሠ እረኛና መጋቢ፣ የተካነ ቀዳሽ፣ የተሾመ አስተዳዳሪ፣ እውቀት የተሰጠው አልሚ እና ከትውልድ ወደ ትውልድ በዘለቄታዊነት አሸጋጋሪ መሆኑንን የሚያጸና ርእዮት፣ መዋቅር፣ አስተሳሰብና ሕግ ለመመሥረት መሥራት ክርስትና መሆኑን እርግጠኛ መሆን።

ሥልጣን የሚይዙ ሰዎች ሕዝብን የሚመሩት ሕዝቡ በዘመናት ውጣውረድ፣ ሃይማኖታዊና ባህላዊ መስተጋብር፣ በአጥንትና በደም የመሠረታቸው እሴቶች፣ ታሪኮች፣ ሕዝባዊ የአስተዳደርና የፍትሕ ሥርዓቶችን ለማክበር፡

ሀ. በግልፅ በማያሳማ ሁኔታ በአደባባይና በጽሑፍ ቃል የሚገቡ፣

ለ. አገር-ፈለቅ እውቀቶችንና እውቀቶቹ የሚገለጡባቸው መዋቅሮችን የሚያከብር፣ የሚያለማና የአገሪቱ የፖሊሲና የትምህርተ አካል ላመድረግ ቁርጠኛ መሆናቸውን በአደባባይና በጽሑፍ ቃል የሚገቡ፣

ሐ. የፖለቲካ መርሆዎቻቸው ከአገራዊ እምነቶችና ባህሎች ከፈለቁት እሴቶች ጋር መስማማቱን፣ እነዚህንም እሴቶች ዜጎች በግልጽ ክርክርና ምርምር ፈትነው ሳይቀበሉት በጭፍን ገልባጭነት ከባዕዳን እየቀዳ በሕግ፣ በፖሊሰ፣ በመደበኛ ትምህርት፣ በመገናኛ ብዙኃንና በኪነትበብ በኩል እንደማይጭንብን ዋስትና የሚሰት ፖሊሲ ያለው

በዚህ መሠረት ኦቶዶክሳዊያን ሁሉ በቋንቋና በሌሎች ከክርስትና አንፃር ሲታዩ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ መቀመጥ የሚችሉ የማንነት መስፈርቶችን ወደኃላ ትተን ለነፍስም ለሥጋው ዋስትና በሚሆነን በጥምቀት ከሥላሴ ባገኘነው የልደታችን የክርስቶሳዊ አንድነት ማንነታችን ያለመከፋፈል በመቆም---- የሚከተሉትን መስፍርቶች ለዘንድሮ ምርጫ መመዘኛ ማድረግ ይጠቅምናል፡-

ሰለዚህ መመርጥ የሚገባን ግለሰብ እና ፓርቲ፡-

1) እውነተኛውን የኢትዮጵያን ታሪክ ከፖለቲካ ትርክት ሰለባነት አውጥቶ በጊዜና በቦታ ሳይከፍልና ሳያጣምም እውነቱን የሚቀበልና የሚመሰክር።
2) በዙ ብሎ ከሐሰተኞችና ከግፈኞች ጋር የማይቆም፣ አነሱ ብሎ እውነተኞችን የይገፋ የፖለቲካ መርህ ለው።
3) በማትከፋፈል አንዲት ኢትዮጵያ ሕልውና የሚያምና እምነቱን ለማስከበር ግልፅ ፖሊሲ ያለው
4) በሰው ልጅ እኩልነት የሚምን እና ዜጎችን በቦታና በቋንቋ እየከፋፈለ ልዩ ትቅመ የሚገባቸውና ጥቅም የሚነሳቸው ብሎ በአንድ አገር ልጆች መካከል ልዩነት እንደማያራምድ በግልጽ ፖሊሰ ያለው
5) የኢ.አ.ተ.ቤ.ክ. የኢትዮጵ መሥራች፣ ጠባቂና እናት እንጂ እስከአሁን በጦረነት ሽንፈት ያጋጠማቸው የአወሮጳ ቀኝ ገዥዎች ባስተማሩት ትምህርት አንጻር ኦርቶዶክስ ወራሪ፣ የጭቆና መሣሪያ፣ የነፍጠኛ እምነት፣ የነግሥታት ተታይ የሚለውን የሀሰት ክስ በአደባባይ የሚየዋግዝ፣ ከትምህርትና ከትርክቶች ሁሉ የሚሠርዝ
6) ቤተክርስቲያንና ልጆቿ አሁን የደረሰባትን መገለልና አድልዎ በአደባባይ የሚያምን እና ለማስቆም በአደባባይና በፖለቲካ ፖሊሲው ገልፆ የሚያሳይ
7) በኢትዮጵያ በዜጎች መካከል የእምነቶች እኩልነትን የሚቀበልና በባዕዳን የፖለቲካ የመልክዐ ምድራዊ ፖለቲካ ተዋኒያን ፍላጎቶች የማይናወፅ አቋም የሚያራምድ
8) አሁን ያለውን በብሔር ነፃ አውጭዎች የተጻፈና ለእልቂት የዳረገንን ሕገ መንግሥት ህዝባዊ በሆነ ሕገ መንግሥት ለመቀየር የወሰነ፣ እና የኢትዮጵያዊያንን ነባር ብዝኃ ማንነቶች በሚሸከም ጋርዮሻዊ እሴትን ባገናዘበ ሌላ ሕገ ሕዝብ እንደሚቀየር በይፋ የሚቀበል
9) ፍትሕን ለማስፈን ቁርጠኛ የሆነ፤ በፖለቲካ ርእዮት ሰበብ በፍትሕ የማይደራደር፤
10) እስከ ዛሬ ድረስ በኦረቶዶክሳዊያን ላይ በስነ ልቦና፣ በአካል፣ በሀብት ድልድል፣ በፍትሕ እጦት፣ በመፈናቀል፣ በመገደል፣ ወዘተ የደረሱ ጉዳቶችን የሚያምን፣ በጥናት መዝኖ በህግ ፍትሕ

ለመስጠት፣ ጉዳቶቿችን ለመካስ፣ አጥፊዎችን ለመቅጣት ቁርጠኛ መሆኑን በቃልኪዳን የሚያረጋግጥ

11) የዜጎችን የኑሮ ደረጃ ያለአድልዎ ፍትሓዊና ተደራሽ ለማድረግ የቆረጠ

12) የዜጎችን ማኅበራዊ ልማት (ትምህርት፣ ጤና፣ ማኅበራዊ መዋቅራት) በኢትዮጵያዊ መሥፍርትና ከኢትዮጵያዊያን እሴት ጋር በሚስማማ መለኪያ ለማሳካት በተጠያቂነት ቃል የሚገባ

13) የፖለቲካ ርእዮትና ሥርዓት የኢትዮጵያን ታሪክ፣ የጋራና ብዝኃ እሴቶችና እምነቶች፣ ባህልና አኗኗር ያገናዘበ ለማድረግ ቃልኪዳን የሚቀበል።

14) ኢትዮጵያዊ ባህልና እምነት አክብሮ መከባበርን፣ ተዋረዳዊ ግኑኝነትን፣ ቅድስናን፣ ታማኝነትን፣ መረዳዳትንእና ማኅበራዊ ግኑኝነትን ለማጠናከር ፖሊሲ ያለው

15) ግልፅነት ያለው የኢኮኖሚ፣ የልማት፣ የንግድ ሥረዓትን በመዘርጋት በዜጎች መካከል አድልዎ የማያደርግ፣

16) በውጭ ግኑኝነቱ ሁሉ አገርን በባዕዳን ላይ ጥገኛ የማያደርግ፣

ከላይ የተዘረዘሩትን በአጭሩ በምሥል ለማስታወስ፡- ማንነታችን የሚያከብርና የሚያስከብርና፣ እሴታችን የአገራችን የሥነ መንግሥት ፍልስፍና አካልየሚደርግ፣ እስከ አሁን ለተፈጸመብን እና እንዲፈጸምብን ላደረገው ርእዮተዓለምም ሆነ መዋቅር መፍትሔ የሚሰጥ ፖለቲከኛ፣ ፓርቲ፣አስተሳሰብና ፖሊሲ ያለውን መምረጥና በተቃራኒው ያለውን መቃወም የቀጣዩ አገራዊ ምርጫ አጠቃላይ የኦርቶዶክሳዊያን መርህ ይሁን!

